# *አንድነት ፓርቲና የመድረኩ ስብስብ አሁን ያላቸውና ወደፊት ሊኖራቸው የሚችል ግንኙነት*

**በያዕቆብ ኃ/ማሪያም (ዶ/ር)**

*ይህ መጣጥፍ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት በሚኖሩ ውሱን በሆኑ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) አባላትና ደጋፊዎች ዘንድ መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ (መድረክ) የተባለው ስብስብ ምንነት፤ አሁን ምን እያከናወነ መሆኑን፤ ወደፊት አንድነት ፓርቲ ከመድረኩ ጋር ሊኖረው የሚችለው የግንኙነት ወርድና ጥልቀት በተመለከተ መጠነኛ ብዥታና ውዥንብር ለማጥራት ይረዳል በሚል የቀረበ ማብራሪያ ነው፡፡*

## 1. *መድረክ ምንድነው ?*

*መድረክ ስሙ እንደሚገልፀው አሁን በሚገኝበት ሁኔታ ለምክክር ብቻ የተቋቋመ*

- *የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት፤*
- *የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፤*
- *የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት፤*
- *የዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉዓላዊነት፤*
- *የአንድነት ዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ፤*
- *የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄን፡፡*

*በተጨማሪም የቀድሞ የአገሪቱ ፕሬዚዴንትና የመከላከያ ሚኒስትሩን የሚያጠቃልል የፓርቲዎችና የሁለት ግለሰቦች ስብስብ ነው፡፡ (የፓርቲዎች የስም ዝርዝር ቅደም ተከተል ፓርቲዎቹ ከስብስቡ ጋር የተቀላቀሉበት ቀንን ያመለክታል) በአሁኑ ወቅት መድረክ አንድ ሕጋዊ ተቋም ወይንም ድርጅት ነው ማለት አይቻልም፡፡ የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2008 አንድ ማንኛውም ስብስብ የፖለቲካ ድርጅት ሆኖ መንቀሳቀስ የሚችለው ሕጉ የሚጠይቁትን ቅድመ ግዴታዎች* (Formalities) *አሟልቶ በምርጫ ቦርድ ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲሰጠው ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም መድረክ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑ ቀርቶ ድርጅት ወይንም ፓርቲ ለመሆን ማመልከቻ እንኳን ያላስገባ ስብስብ ነው፡፡*

*በአሁኑ ወቅት በስብስቡ ተሳታፊ የሆኑት ድርጅቶች ሙሉ ሕጋዊ ህልወናቸው ጠብቀው ከሉዓላዊነታቸው ምንም ቀንሰው ለመድረክ ያልሰጡ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው በምርጫ ቦርድ ተመዝግበው ሰርተፊኬት የጨበጡ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው፡፡*

*መድረኩ ከተቋቋመ ማለት ፓርቲዎቹና ግለሰቦቹ በስብስብ ለመገናኘትና ለመመካከር ከወሰኑ ከስምንት ወራት በልጦአል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ እነዚህን ፓርቲዎችና ግለሰቦችን ብቻ የሚገዛ (አንድነትን ሳይጨምር) አንድነት ፓርቲ ገና መርምሮ ይቀበለው አይቀበለው እንደሆነ የማይታወቅ የውስጥ አሠራር ደንብ አውጥተው ይፋ አድርገዋል፡፡ አንድነት ፓርቲ ያልተሳተፈባቸው ስብስብ ፓርቲዎቹ በአገሪቷ ወቀታዊ ሁኔታ አንዳንድ መግለጫዎችንም አውጥተዋል፡፡ በመጨረሻም አንድነት ፓርቲ የተሳተፈበት የካቲት 12 ቀን 2001 የፖለቲካ ምህዳሩ መጥበብ፤ በፕሬስ አባለት ላይ የሚደርሰው ወከባና እሥር፤ የመከላከያ ሠራዊታችን*

ከሶማሊያ መውጣት በተለይም የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ሕገ-ወጥ ድጋሚ እስር በአጽንኦት በማውገዝ ሊቀመንበራችን በአስቸኳይ አንድትፈታ ጠይቋል።

## 2. አንድነት ፓርቲ ከሙድረኩ ስብስብ ጋር ለመሥራት የወሰነበት መንስኤው፤

በአገራችን የተንሰራፋው የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ዴሞክራሲያዊና ሠላማዊ በሆነ ትግል ተፋልሞ ለድል ለመብቃትና መድብለ ፓርቲ ሥርዓት ለመመሥረት ብሎም ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት ለማስረገጥ ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት የተቀበሉ በጥቅሉ ዴሞክራሲን መርሆአቸው ያደረጉ እውነተኛና ሀቀኛ የገገር ፓርቲ ተቃዋሚነታቸው ያስመሰከሩ ፓርቲዎች በተስማሙበት በጋራ ፕሮግራም ዙሪያ ማስተባበር አማራጭ የሌለው የትግል ስልት መሆኑን ፓርቲያችን ያምናል። በገንዘብ የበለጸገ፤ በሰው ኃይል (በካድሬዎች) የዳበረ ለ18 ዓመታት ያለተቀናቃኝ በሥልጣን ላይ ተፈናጥጦ የቆየ ፓርቲ ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ትግል መለወጥ የሚቻለው በተቃዋሚዎች ሕብረት ብቻ መሆኑን የሌሎች አገሮች ተሞክሮች በተደጋጋሚ አረጋግጠዋል። ይህንን በመገንዘብ ነው የፓርቲያችን ፕሮግራም መግቢያ ተራ ቁጥ 5 በአገራችን ዴሞክራሲ እንዲሰፈን የሕግ የበላይነት እንዲከበር «. . . የሁሉም በሕጋዊና ሠላማዊ ትግል ለመሳተፍ የቆረጡ የፖለቲካ ኃይሎች ትብብር እንደሚጠይቅ አሳስቦአል። በመቀጠልም «የእነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች የትብብር መድረክ እንዲፈጠርና የተጀመረም ካለ እንዲጠናከር ፓርቲያችን የበኩሉን ሁሉ» እንደሚያደርግ ያረጋግጣል። የፓርቲው ፕሮግራም ለማስፈፀም ኃላፊነት ያለበት የሥራ አስፈፃሚው አካል ይህንን የተጣለበት ግዴታና ኃላፊነትን ለመወጣት ነው በመድረክ ዙሪያ ከተሰባሰቱት ፓርቲዎችና ግለሰቦች ጋር ለመሥራት ወስኖ ውሳኔው በብሔራዊ ምክር ቤት እንዲጸድቅ ያደረገው።

## 3. የአንድነት በመድረክ ዙሪያ ከተሰባሰቡት ፓርቲዎችና ግለሰቦች፤ ጋር ያከናወኗቸው ተግባራት፤

ሀ/ ፓርቲዎቹና ግለሰቦቹ በመድረክ ዙርያ ተሰባስበው አንድ የምክክር ቡድን ያቋቋሙበት በምስረታው ስብሰባ አንድነት ፓርቲ እንዲገኝ ተጋብዞ የአንድነት ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰኔ 16 ቀን 200 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት በታዛቢነት ተገኝቶአል። ስለስብሰቡ መፈጠርና ስለአንድነት ፓርቲ በታዛቢነት መገኘት በመገናኛ ብዙሃን ሰፊ ሽፋን ተሰጥተታል።

ለ/ ፓርቲያችንን ለሕዝብ ለማስተዋወቅ ህዳር 27 ቀን 2001 ዓም ብዙ ሺህ ሕዝብ በተገኘበት በመብራት ኃይል አዳራሽ ስብሰባ በመድረኩ ዙሪያ የተሰባሰቡት ፓርቲዎች ተወካዮችና ግለሰቦች በስብሰባው ተገኝተው ንግግሮች በማድረግ ለስበሰባው ውጤታማነት አስተዋጽኦ አድርገዋል። አሁን በእስር ላይ የመትገኘው ሊቀመንበራችን አንድነት ፓርቲ ከመድረኩ ጋር አንደሚሠራ በጊዜው ለተሰብሳቢውን አብስራለች።

ሐ/ ታህሣሥ 18 እና 25 ቀን 2001 ዓም መድረኩ ባዘጋጀው በኢምፔሪያል ሆቴል በተካሄደው የሁለት ቀናት ሕዝባዊ ውይይት ፓርቲያችን ተጋብዞ አባላትና የአመራሩ አካል ተገኝተዋል።

መ/ የፓርቲያችን ሊቀመንበር ከታሰረች ከጥቂት ቀናት በኋላ የመድረኩ አባላት እሥራቱን አውግዘው በአስቸኳይ እንድትፈታ ሁሉም በአንድነት ጠይቀዋል፡፡

ሠ/ የፓርቲያችን ሊቀመንበር የወ/ት ብርቱካን ሕገ-ወጥ እስር ለመቃወም በተደረገው የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዓት ላይ የስብስቡ ተወካዮች ተገኝተው ለበአሉ ድምቀት ሰጥተውታል፡፡

ረ/ ከላይ የተጠቀሰው የካቲት 12 ቀን 2001 ዓም በተለይ የሊቀመንበራችን መታሠር አውግዞ በአስቸኳይ እንድትፈታ የሚጠይቅ መግለጫ የስብስቡ አባላት አውጥተው እያንዳንዱ ፓርቲ አንድነትም ጭምር ማህተም አሳርፎበታል፡፡

ሰ/ ፓርቲያችን በስብስቡ እንዲወክሉት ሦስት የሥራ አስፈፃሚ አባላትን ሲመድብ አባላቱ በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ ተደልድለዋል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ የስብስቡ ፓርቲዎች አባላትና ግለሰቦቹ የሚገኙበት ግብረ-ኃይል የተቋቋመ ሲሆን ግብረ-ኃይሉ ሥራውን የሚጀምረው ከዜሮ መሆኑን የአንድነት ተወካዮች አስምረውበት ሃሳቡ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ግብረ-ኃይሉ ተግባሩ መለስተኛ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለፓርቲዎቹ ቀርቦ ፓርቲዎቹ በፓሮግራማቸው በተደነገገው መሠረት (አንድነትን አስመልክቶ በምክር ቤቱ) ካፀደቁት በኋላ የስብስቡ ማኒፌስቶ ይሆናል፡፡ በመለስተኛ ፕሮግራም የሚካተቱ ጉዳዮች ስለ ሰብአዊ መብቶች፤ ስለ እምነት ነፃነት፤ ስለ መደራጀት መብት፤ የመሰብሰብና የመደራጀት መብት፤ የመሰብሰብና ሠልፍ የማድረግ መብት፤ የበሔር-ብሔረሰቦች መብት፤ የሕግ የበላይነት የመንግሥት አወቃቀር ወዘተ የመሳሰሉትን ሲሆኑ እስከ ዛሬ በተጠናቀቀው ሂደት ስለሰብአዊ መብት፤ ስለ እምነት ነፃነት፤ ሃሳብን በነፃ ስለመግለጽ መብት ስለመሰብሰብና ሠልፍ ስለማድረግ ግብረ-ኃይሉ ተነጋግሮ ሁለም ተሳታፊዎች ተመሳሳይ አቋም እንዳላቸው ሊገነዘቡ ችለዋል፡፡

## 4. የመድረኩ አሠራርና ውሳኔ አሰጣጥ፤

የፓርቲዎች ተወካዮችም ሆነ ግብረ-ኃይሉ ስብሰባ በሚያደርጉበት ወቅት ሥርዓት ያለው ውይይት ለማድረግ ስብሰባውን የሚመራ አንድ ሊቀመንበር የግድ ይላል፡፡ በዚህም መሠረት የፓርቲዎች ተወካዮች ስብሰባ በሚያካሂዱበት ወቅት ስብሰባዎቹን ለመምራት አንድ ፓርቲ ለአንድ ወር በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡ ግብረ-ኃይሉ ደግሞ በየሁለት ስብሰባዎች ከየፓርቲዎቹ በተራ አዲስ ሊቀመንበር ይሰየማል፡፡ በማንኛውም አርእስ ላይ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኋላ እንደሌላ ማንኛውም ስብሰባ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ አይወሰንም፡፡ እያንዳንዱ የፓርቲ ወኪል ለሌሎች ውሳኔ ወይንም አቋም ተገዥ አይሆንም፡፡

## 5. መድረኩ የሚኖረው ሕጋዊ ተቋምነት፤

የመድረኩ ስብስብ መለስተኛ ፕሮግራሙ ከተቀበሉና ካፀደቁ መድረኩ ምን አይነት ሕጋዊ ተቋም ይሆናል፡፡ የሚለው ጥያቄ ወሳኝነት ያለው ነው፡፡ ማንኛውም የስብስቡ አባል ፓርቲ መለስተኛ ፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ የማይቀበል ከሆነ ከመድረኩ ስብስቦች ጋር ያለው ግንኙነት ይቋረጣል ማለት ነው፡፡ ወይንም አንድ ፓርቲ ያልተስማማባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ሆኖ በተስማማባቸው ጉዳዮች ብቻ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ትብብሩን ለመቀጠል ይችል ይሆናል፡፡ በአንድነት ፓርቲ ሕገ-

ደንብ መሠረት ይኸ የሚወሰነው በሥራ አስፈፃሚው ሆኖ ውሳነው በብሔራዊ ምክር ቤት መጽደቅ ይኖርበታል።

ከላይ እንደተገለፀው መድረኩ አሁን ባለበት ሁኔታ ሕጋዊ ሰውነት የሌለው ሊከስም ሆነ ሊከሰስ የማይችል ንብረት ለመያዝም ከመንግሥስትም ሆነ ከሌላ ሦስተኛ አካል ጋር ሊደራደር ወይንም ስምምነት ሊፈጽም የማይችል የፓርቲዎች ስብስብ ነው።

መድረኩ እንደ ፖለቲካ ድርጅት  መንቀሳቀስ ከፈለገ የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ በሚደነግገው መሠረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሦስት የአደረጃጀት ቅርጽ መያዝ ይኖርበታል።

ሀ/ <u>ውሁድ ፓርቲ</u>

በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡ ፓርቲዎች ሁለም ወይንም በከፊል ህልውናቸውን ሠርዘው በአዲስ ስምና መዋቅር የቀድሞ ፓርቲዎች መብትና ግዴታ ለአዲሱ ፓርቲ አውርሰው አንድ ወጥ ውሁድ ፓርቲ ሊሆኑ ይችላሉ።

ለ/ <u>ግንባር</u>

በመድረኩ የተሰባሰቡት ፓርቲዎች ሁሉም ወይንም ጥቂቱ ብቻ የየራሳቸው ፕሮግራም፤ መተዳደሪያ ደንባቸው፤ ስማቸውና የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤ የየራሳቸው ሀብትና ንብረት፤ አባሎቻቸውንም እንደያዙ ለተወሰኑ ዓላማዎች አብረው እንዲንቀሳቀሱ ግንባር ሊፈጥሩ ይችላሉ።

ሐ/ <u>ተቀናጅቶ መንቀሳቀስ፤</u>

ሁለት ወይንም ቁጥራቸው ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተወሰነ ጊዜ በተወሰኑ ጉዳዮች በመሪዎቹ አማካይነት ስምምነት ሊደርሱ ይችላሉ። ሕጉ እንደሚደነግገው ፓርቲዎች ለመዋሀድ ሲወስኑ ወይንም ግንባር ለመፍጠር ሲስማሙ ውህደቱ ወይንም ግንባር የመፍጠሩ ውሳኔ በጠቅላላው ጉባኤ መጽደቅ አለበት። ተቀናጅቶ ለመንቀሳቀስ ግን የፓርቲዎቹ ከፍተኛ አመራር ስምምነት በቂ ይሆናል።

## 6. <u>ማጠቃለያ፤</u>

በአሁኑ ወቅት በመድረክ ዙሪያ ተሰባስበው የሚመካከሩ ፓርቲዎች ሕግ የሚያውቀውና ፓርቲዎቹ ላይ ተፈፃሚነት ወይንም አሳሪ የሆነ ያከናወኑአቸው ምንም ዓይነት ተግባራት የሉም። እስከ ዛሬ ፓርቲዎቹ  የተፈራረመአቸው አሳሪ የሆኑ ምንም አይነት የውል ሠነዶችም የሉም። «አንድነት ፓርቲ ከመድረኩ ስብስብ ፓርቲዎች ጋር ተቀላቀለ» የሚለው ሀረግ በአንዳንድ አካባቢዎች ያልሆነና ያልታቀደለት ትርጉም ተሰጥቶታል። ጨዋታ ለመጨወትም ይሁን አብሮ ለመብላት ወይንም ውይይት ለማድረግ ቀድመው ከነበሩት ጋር መቀላቀል ያስፈልጋል። «መቀላቀል» የሚለው ቃል በዚህ ትርጉሙ ሕጋዊ ድርጊት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም መቀላቀል የሚያስችል መድረክ የሚባል በሕግ የታወቀ ተቋም  የለምና። አንድነት

ፓርቲ መድረክ ውስጥ ገባ ማለትም አይቻልም። ምክንያቱም አሁንም አንድነት ፓርቲ የሚገባበት ሕግ ያወቀው ተቋም የለም።

አንድነት ፓርቲ በመድረኩ ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ጋር መተዳደሪያ ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት ቢሻው ሕልውናውን አጥፍቶ ሊዋሃድ፤ ቢሻው ግንባር ሊፈጥር፤ ወይንም በአንዳንድ ጉዳዮች ብቻ ሊተባበር፤ ወይንም ብቻውን ትግሉን ለመቀጠል የሚያስችለው ምርጫው በምንም መልኩ አልተነካም። ይህንንም ሊወስን የሚችለው ምክር ቤቱ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው ሲያፀድቀው ብቻ ነው።